# ፌዴራል ኢትዮጵያ ወዴት፡......

**ከሀረግ- 03-01-18**

የጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ ከመንግሥትና ከኢህአደግ ሀላፊነታቸው በራሳቸው ፍቃድ ለመልቀቅ ያቀረቡትን ጥያቄ ተከትሎ የአገራችን የፖለቲካ ትኩሳት የጨመረ ይመስላል፡፡ የለውጥ ሰሞን ብዙ ወገን ወደ ፖለቲካ መሳቡ የማይቀር እውነታ በመሆኑ ሁሉም ወገን የየራሱን ፍላጐትና ዝንባሌ መሠረት በማድረግም ስለ መፃኢ ኢትዮጵያ ጥያቄ ሲሰነዝር ይደመጣል፡፡ የብዙዎቹ ጥያቄ የሚያጠነጥነው አገራችን ወዴት እያመራች ነው የሚለው ነው፡፡ የአንዳንዶቹ ጥያቄ ለወገን ከመቆርቆር እና የተጀመረውን የፀረ-ድህነት ትግል ወደ ኋላ እንዳይመለስ ካላቸው ሥጋት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአንጋሽነት መብት የተሰጣቸው የሚመስላቸው ቀጣዩ መሪ ከዚህ ወይም ከዛኛው ብሄር ካልሆነ ብለው የሚከራከሩ ወገኖችም ተበራክተዋል፡፡ ከፊሎቹ ግን ወንዝ ሲደፈርስ ትልቅ አሳ ይገኛል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአገር ቤት የሚታዩ የፖለቲካ ይሁን የኢኮኖሚ ለውጦች ከማይዋጥላቸው ወገኖች የሚመነጭ አስተያየት ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ሁሉንም ከዜሮ ለመጀመር በአገር ቤት የተጀመረው ግንባታ ከመሠረቱ መውደም አለበት የሚል አጀንዳ ይዘው አቧራው እንዳይረግብ ነዳጅ የሚያርከፈክፉ ናቸው፡፡

ይህ ጽሁፍ ከጠቅላይ ሚኒስትር የፖለቲካ ውሣኔ የጀመረው ትኩስ ከሚባሉ የፖለቲካ ወሬዎች አንዱ በመሆኑ እንጅ ለአገራችን ፖለቲካ መሠረታዊ ጉዳይ ሆኖ አይደለም፡፡ ለነገሩ በአገራችን በቅርብ ቀናት ከታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅም መጀመር ይቻል ነበር፡፡ ቁምነገሩ ግን እነዚህ ጉዳዮች በአገራችን በተጀመረው የለውጥ ሂደት የተከሰቱ ክስተቶች እንጅ በፖለቲካ ምሕዳሩ እና በአገር ደረጃ እየተፋለሙ ከሚገኙ የፖለቲካ ቅራኔዎች አንፃር ሲታይ ኢምንት ናቸው፡፡

## የአገራችን የወቅቱ መሠረታዊ የፖለቲካ ቅራኔዎች

በአሁኑ ወቅት በአገራችን የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትግል በይዘቱ አዲስ አይደለም፡፡ ከአገራችን የፖለቲካ ኢኮኖሚ በሥልጣን ላይ የሚገኘው ገዠ ፓርቲ የሚወክላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች አሉት፡፡ በሥልጣን ላይ ያለው ኢህአድግ አገራችንን የብሄር ብሄረሰብ የጋራ መኖሪያ ናት የሚል መነሻ ያለው ሲሆን፤ በአገሪቱ የተቀረፀው ሕገ መንግሥትም ዲሞክራሲያዊ ህብረ ብሄራዊነትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ታግለዋል፡፡ ይህ ሕገመንግሥት በዋነኛነት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የትግል ውጤት ቢሆንም ኢህአድግም እንደ ድርጅት የታገለለት በመሆኑ በቅርቡ ይመለከተዋል፡፡ የኘሮግራሙ አንኳርም ጭምር ነው፡፡ ገዠው ፓርቲ የሚያራምደው የኢኮኖሚ ፖሊሲም ዋነኛ የትግልና የልዩነት ነጥብ ነው፡፡ በአገራችን ያለው የወቅቱ ፖለቲካና የሀይል አሰላለፍም እነዚህን መነሻ በማድረግ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ኢህአድግ ልማታዊ መንግሥት የእድገት አቅጣጫ

በመከተል የሊበራል አማራጭ አልተቀበለም፡፡ በአገራችን የፖለቲካ ኢኮኖሚ ያለው ትልቁ ቅራኔም በሊበራሊዝም ስም በተሸፈነው የኪራይ ሰብሳቢ የፖለቲካ ኢኮኖሚና በልማታዊ መንግሥት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሆነዋል፡፡

በአገራችን በአሁኑ ወቅት ያለው የሀይል አሰላለፍም ከዚሁ የመነጨ ነው፡፡ የልማታዊ መንግሥት የፌዴራል ሥርዓቱን የሚቃወሙ በአንድ ግንባር ተሰልፈው በኢህአድግ ላይ የተባበረ ክንዳቸውን ለማሳረፍ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ ሀይሎች የሚያስተሳስራቸው የጋራ ጥቅም እንጅ የጋራ አላማ አላቸው ለማለት አይቻልም፡፡ ሁሉም ወገኖች ከኢህአድግ መዳከም የሚገኘውን ትርፍ ለማግበስበስ የሚሯሯጡ እንጅ ሜዳው ለእነሱ ብቻ ቢተው አጥንት እንዳገኙ ውሾች እርስ በርስ የሚናከሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሃይሎች ከሩቅ የመጡ ወይም በምናብ የምንስላቸው ሳይሆኑ በኢህአድግ ውስጥም ተሰግስገው ድርጅቱ ወደ ፊት እንዳይራመድ ቀዝፈው የያዙት   ጭምር ይገኙበታል፡፡ በየመንደሩ የሕዝብ ሀብት የዘረፉ፤ በሕዝብ ሀብት ያተረፉ፤ ነገር ግን በየእለቱ የሕዝብ ጥያቄ ሲገጥማቸው መመለስ የማይችሉ በየእለቱ ኢህአድግን የሚቦረቡሩ ወገኖችም ጭምር ከውጭ ከሚገኙ ጽንፈኞች ጋር በማበር ግንባር ፈጥረው እየታገሉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች በአሁኑ ወቅት ኢህአድግ ራሱን ለማጥራት የጥልቅ ተሀድሶ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የዚሁ ፍፃሜ በውስጡ የተሰገሰጉትን በማጥራት አሰላለፉን ያስተካክላል የሚል ተስፋ አለ፡፡ የኢህአድግ ሰንጐ የያዘው በአመለካከት ስለተሸረሸረ ነው የሚለው ግምገማ ዞሮ ዞሮ በውስጡ የአሰላለፈ ችግር ተከስቶ እንደነበረ ይጠቁማል፡፡ በዚሁ የሃይል አሰላለፍም ላይ የኒዮ ሊበራል ሃይሎችና የአገራችን ታሪካዊ ጠላቶችም በዚሁ ግንባር ተሰልፈው እናገኛቸዋለን፡፡ በአገር ቤት የሚካሄዱ ረብሻዎች የሚመሩትና የፈንድ አስተላለፊዎችም ለኢትዮጵያ ጠላቶች ያደሩ ወገኖች ናቸው፡፡

## <u>የአገራችን መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎች</u>

በአሁኑ ወቅት በሁለት ጐራ በመከፈል እያወዛገበ ያለው መሠረታዊ ጉዳይ የብሄር ብሄረሰቦች ጥያቄ በሕገ መንግሥቱ የተፈታበት አቅጣጫ አሁንም ዋነኛው የልዩነትና የአንድነት አጀንዳ ነው፡፡ ሕገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ ያደረገው ለአንድ ምእተ አመት ይህል የቆየውን የማንነት ጥያቄ ምለሽ በመስጠቱ ነው፡፡ የብሄር ብሄረሰቦች የእኩልነት ጥያቄ ብዙ ወገኖች ከፖለቲካ ድርጅቶች አልፎ ተርፎም ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ጋር ያያይዙታል፡፡ አንዳንዶቹም ከጆሴፍ ስታሊና የተቀዳ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ በእኔ በኩል ይህ ጉዳይ ከዚሁ የሰፋና ጥልቀት ያለው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ አካል ነው፡፡ የብሄር ጥያቄ ማንም ሰው ወይም ቡድን አምጦ ሊወልደው የሚችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ጥያቄ ማንም በምድር ላይ ያለ ሃይል ሊያፍነው እንደማይችል ታይተዋል፡፡ የብሄር ብሄረሰብ ጥያቄ የአገራችን ማሕበራዊና ፖለቲካዊ እውነታ የወለደው ነው፡፡ አገር ግንባታ ሲጀመር የሌሎችን ማንነት በማጥፋት የተዋሀደች አገር ለመፍጠር የተደረገው ጥረት የማያባራ ቅራኔ ወልዷል፡፡ ቅራኔውን በመደብና በብሄር ቅራኔ መልክ ተከስተዋል፡፡ ብዙ የፖለቲካ ቡድኖችም እነሰም በዛ በአንድ ወይም

በሌላ መልክ በፕሮግራማቸው ለማቀፍ ሞክረዋል፡፡ በአገራችን ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለማስተናገድ ያልቻለ የፖለቲካ ቡድንም ሊሳካለት አይችልም፡፡ የእስካሁን ታሪካችን የሚያመለክተው የብሄሮች የእኩልነት ጥያቄ ያልተቀበለ የፖለቲካ ቡድን በሂደት እየጨነገፈ ሲሄድ ብቻ ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ በሥልጣን ላይ ያለው ኢህአዴግ በተቃዋሚው ወገን የሚቀጠቀጠው የብሄር እኩልነት በማስፈኑ ነው፡፡ አሁን እየተገነባ ያለውን የፌዴራል ዲሞክራሲ የሚደግፉ ሀይሎች በአገር ውስጥም በውጭም እንዳሉ የሚታወቅ ነው፡፡ ነገር ግን በውጭ የሚገኙ ብዙዎቹ ዲሞክራቶች መድረኩን ለጽንፈኞች በመተው በትዝብት ለመከታተል የመረጡ ይመስላል የፌዴራል ሥርዓት የቀድሞ ገዠዎች አስተሳሰብ ባላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲሁም በየብሄሩ ገዠ መደብ ሆነው በመውጣት የአገራችን ገዠ መደብ ለመሆን ከሚመኙ ጠባቦች ለመታደግ አቅም ያለው ሕብረተሰብ ሰፊ ነው፡፡ የዲያስፖራ ወገኖችም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በሁሉም መስክ በምንፈልገው መንገድ እየሄደ ነው ማለት ባንችልም መሠረታዊ የብሄር እኩልነት ላይ በጋራ የምንሰለፍበት እድል እንኳ ለማየት አቅቶናል፡፡

## <u>የኢህአዲግ ሥልጣን የማን ሥልጣን!</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርአት የሥልጣን አወቃቀር በአገራችን የፖለቲካ ሥርአት መሠረታዊ ለውጥ አስከትለዋል፡፡ የሥልጣን ፍሰት ከቀድሞ ዘመን ተቀይሮ ፍሰቱ ከታች ወደ ላይ ሆነዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርአት የሥልጣን ባለቤቶች ብሄር ብሄረሰቦች መሆናቸውን ሕገመንግሥቱ አረጋግጦዋል፡፡ የፌዴራል መንግሥት የሚያስተዳድረው ሥልጣን የተሰጠው ከክልሎቹ ተቆርሶ ነው፡፡ በመሆኑም በአገራችን ሕገ መንግሥት የሥልጣን ባለቤት ክልሎች ናቸው፡፡ ከክልሎች ተቆርሶ የተሰጠውን ሥልጣን ለማስተዳደር የተቋቋሙ የፌዴራል ሥርዓት ከሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች በተመጣጠነ ሁኔታ በተመረጡ የሕዝብ ተወካዮች ይተዳደራል፡፡ የሕዝብ ተወካዮችም በሕገመንግሥቱ መሠረት መንግሥት ያቋቁማል፡፡ ሌሎች የመንግሥት ተቋማትም ይኸን በሚያንፀባርቅ ሁኔታ ያቋቁማል፡፡ በዚህ የመንግሥት ግንባታ በቢሮክራሲው፤ በፀጥታ ሀይሎችና በመከላከያ አባላት ለማመጣጠን ጥረቱ እየቀጠለ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ግን የተቃዋሚው ወገን ሥልጣን የህውሓት ነው የሚል ክስ ሲያቀርብ ይደመጣል፡፡ የትግራይ የበላይነት አለ የሚል ክስና ወቀሳ የሕዝብ መዝሙር ያህል ሲደጋገም ይደመጣል፡፡ በጊዜ ቆይታም ይኸ መዝሙር ተቃዋሚዎች ብቻ ሳይሆን አንዳንድ የኢህአድግ አባላትም የተጋሩበት ሁኔታ ተፈጥረዋል፡፡ ይኸ ጉዳይ በአገር ደረጃም ቢሆን አጀንዳ እየሆነ መጥቷል፡፡ አልፎ ተርፎም በአንዳንድ ተቃዋሚዎች በትግራይ ሕዝብ ላይ እልቂት (Genocide) እስከማወጅ ደርሰዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይ በመሆኑ እንጂ እንደ እነሱ ፍላጐት የሕዝብ እልቂት እንዲከሰት ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም፡፡ የተቃዋሚዎች በትግራይ ሕዝብና ህውሓት ላይ የሚያደርጉት ዘመቻ ግን የፌዴራል ሥርዓቱን ለማፍረስ ዓላማ እንዳለው መገንዘቡ አስፈላጊ ነው፡፡

ብዙ የተቃዋሚ ቡድኖች ኢህአድግን ለማሸነፍ በትግራይ ሕዝብ ላይ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ማካሄድ እንዳለባቸው አምነው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ስትራተጅው ህውሓትን ከኢህአዴግ መነጠል የመጀመሪያው ሥራ ነው፡፡ በመቀጠልም ህውሓትን ከትግራይ ሕዝብ መነጠልና ከተቻለም የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነጠል ብዙ ሥራ ሲሰራበት እየተመለከትን ነው፡፡ አንዳንዶቹም የትግራይ ሕዝብ ያለአመክንዮ ለህውሓት ድጋፉን ይሰጣል የሚሉ ቅስቀሳዎችም ሲሰነዘር ይደመጣል፡፡ በአንድ ወቅት መቀሌ ድረስ ሄደው ሕዝብን ያነጋገሩ አንጋፋ ተቃዋሚ የትግራይ ሕዝብ ከአንድ ፋብሪካ የተሰራ ሻሙና አይነት ነው በማለት የተከበረን ሕዝብ ሲያዋርዱት ተሰምተዋል፡፡ የትግራይ ሕዝብ የፈለገውን የፖለቲካ ቡድን የመምረጥ መብት እንዳለው በመዘንጋት ሌሎች ወገኖች ምርጫውን ሊያስተካክሉለት ይሞክራሉ፡፡

በተቃዋሚዎች ጐራ ሲቀነቀን የነበረው ትምክህትና ጠባብነትም በረዥም ጊዜ የዘረኝነት ቅስቀሳ ድንበር ጥሶ የትግሉ ወዳጆች የሆኑት ጭምር ጥያቄ በማንሳት ላይ ናቸው፡፡ የአገሪቱ በጀት እንዴት እንደሚወሰን፤ ክልሎችም ራሳቸውን እንደሚያስተዳድሩ እያወቁም ቢሆን የትምክህተኞችና የጠባቦችን አጀንዳ ሲያነሱ ይደመጣሉ፡፡ በፌዴራል መ/ቤቶች ያለውን የሠራተኞች ስብጥርም አበጥረው ያውቃሉ፡፡ በአገሪቱ ያሉ አበይት ፌዴራል ፕሮጀክቶች የት እንደሚገኙ ያውቃሉ፡፡ መከላከያም የፀጥታ መዋቅር ውስጥ ያሉትም እነማን እንደሆኑ ያውቃሉ፡፡ ሆኖም የተሰጣቸውን በጀት በመጠቀም ሕዝቡን በማንቀሳቀስ ልማት ማምጣት አልቻሉም፤ ለዚሁም ሰበብ ፍለጋ ላይ ያሉ ጥቂት አይደሉም፡፡

የትግራይ ሕዝብ ህውሓት በትምክህተኞችና በጠባቦች ጥርስ የገባበት እነዚህ ሰዎች የሕዝባቸው ወዳጆች ስለሆኑ አይደለም፡፡ የትግራይን ሕዝብ የሚጠላ የአማራ፤ የአፋር ወይም የኦሮሞ ሕዝብ ወዳጅ ሊሆን እንደማይችል እሙን ነው፡፡ በማንኛውም የሀላፊነት ደረጃ በክልልም ይሁን በፌዴራል በሀላፊነት የሚሰራ ግለሰብ ወይም ባለሥልጣን ሕዝቦችን በሙሉ በእኩልነት የማየት ግዴታ አለበት፡፡ ሕዝቦችን በእኩልነት የማይመለከት ግለሰብ የመንግሥት ሀላፊነቱን አስረክቦ መውጣት አለበት፡፡ የኢትዮጵያ የመንግሥት ተቋማት የክልልም ይሁን የፌዴራል ዜጐችን በእኩልነት የማገልገል ግዴታ አለባቸው፡፡

በነገራችን ላይ በሁሉም ወገን ዘንድ መታወቅ ያለበት እውነታ በአገራችን የግንባታ ሂደት ላይ የሚገኘውን የፌዴራል ሥርአት በመቀየር በሌላ ለመተካት ፍላጐት ካለ ከወዲህ እንደማይሆን እና ሊሰራ እንደማይችል መገንዘቡ ጠቀሜታ አለው፡፡ በሕገ መንግሥታችን ላይ የሰፈረውን እኩልነት ተቀብለን መጓዝ ካልተቻለ ያለው አማራጭ አደገኛ መበታተን ይሆናል፡፡ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከእኩልነት ውጭ እጅና እግሩ ታስሮ የሚኖር ሕዝብ ሊኖር የሚችል ሕዝብ አይኖርም፡፡ የመለያየት አማራጭና እድሉ ያለ ቢሆንም ማለቂያ ወደ ሌለው የእርስ በእርስ ጦርነት እናመራ እንደሆነ እንጅ በተጨባጭ የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ዘረኝነት፤ ትምክህትና ጠባብነትን እየተዋጋን እኩልነትን መኮትኮት የግድ ይለናል፡፡ አንዳንድ ወገኖች በትግራይ ሕዝብ ላይ የጥላቻ ዘመቻ ሲያካሂዱ መልሰው መላልሰው ማየት

ያለባቸው ነገር እንዳለ ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች አንድ አካል የሆነውን የትግራይ ሕዝብ የመነጠልና የማዳከም ዓላማ መልሶ አገሪቱዋን በሙሉ የሚጎዳ መሆኑን ማየቱ ይጠቅማቸዋል፡፡ በዚህ ላይ ኢትዮጵያውያን ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶችም ሊታገሉላት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ባለፉት ሁለት አመታት አንዳንድ ገራሚ ነገሮችም የተስተዋሉበት ሁኔታ ተመልክተናል፡፡ አንድ ወቅት የትግራይ ባለሀብቶች በአዲስ አበባ በባለቤትነት ያሰሩዋቸው ሕንፃዎች ብዛት ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች እንደሚበዛ በሰፊት ይነገር እንደነበር እኔም አድምጫለሁ፡፡ ይህ ጉዳይ የኢህአድግ ድርጅቶችም ዘንድ ዘልቆ ኖርዋል ለካ ቆጠራ እንዲካሄድ በመወሰኑ አንድ ቡድን ተቋቁሞ የእያንዳንዱን ሕንፃ ባለቤት ተጣርቷል፡፡ የሚያሳዝነው ግን የትግራይ ባለሀብቶች ያሰሩዋቸው ሕንፃዎች በቁጥር በጣም ሲበዛ አነስተኛ መሆናቸው ሲረጋገጥ የነበረው ዘመቻ የቆመ ቢሆንም ይህ ኘሮፓጋንዳ በአደባባይ አልተጋለጠም፡፡ ይኸ አይነቱ አዝማሚያ በጣም አስደንጋጭ ነው፡፡ አንድ ሰው በቢዝነሱ አለም ገብቶ ለሌሎች በሚፈቀደው አግባብ ሀብት ማፍራት የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን አስተሳሰብ ሲጠነዛ እስከዛ ድረስ ይኬዳል፡፡

በየዘርፉ ያለውን ውንጀላና ክስ በዚሁ ጽሁፍ ማስተባበል አስቸጋሪ ነው፡፡ ይኸ ሆን ተብሎ የተፈበረከ በመሆኑ ማቆሚያ ያለውም አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች ይህንን ጉዳይ ሊታገሉለት ይገባል፡፡ በአገራችን ሕገ መንግሥት የሥልጣን ክፍፍል ግልጽ አድርጎት እያለ ህውሓት የምትህት ሃይል ኖሮት በእንዳንዱ ባለሥልጣን ወንበር በስተጀርባ ሆኖ ለማስተዳደር አይቻለውም፡፡

<u>የፌዴራል ሥርዓት ወቅታዊ ፈተና</u>

በታሪክ ዲሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት የከሸበት አጋጣሚ መኖርን ማወቁ ተገቢ ነው፡፡ የፌዴራል ሕገመንግሥት ዲሞክራሲያዊ ስለሆነ ሊቀለበስ አይችልም የሚል አስተያየት ትክክል አይሆንም፡፡ ሁለት የታሪክ አጋጣሚዎች ለአብነት ጠቃሚ ነው፡፡

በ1919 የተቋቋመው የጀርመን የቫይማር ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት ሂዶ ሂዶ ተቀልብስዋል፡፡ ሕገመንግሥቱ መቀልበሱ ብቻ ሳይሆን በናዚዎች የተተካ መሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ ይኸ የታሪክ ክስተት ያጋጠመው ሕገ መንግሥት መደገፍ የነበረባቸው የፖለቲካ ቡድኖች እርስ በእርስ ወደ ትርምስ ስለገቡ ነው፡፡ አንዳንድ ፓርቲዎች የእነሱ ድል በሌላኛው ኪሳራ ያገኛል ብለው በማስላታቸው ነው፡፡ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ማለት ነው፡፡ በመጨረሻም ናዚዎች ወደ ሥልጣን ሲወጡ ሁሉም ፓርቲዎች ሰለባ ሆነዋል፤ አገሪቱም ጭምር፡፡ በፈረንሣይ በ1849 - 1851 የነበረው ታሪካዊ ክንዋኔም ተመሣሣይ ሁኔታ ውጤት ነበረው የፖለቲካ ቡድኖች እርስ በእርስ ሲራኮቱ በመጨረሻ ግን የነበረው ፓርላማ ራሱን አጠፋ፤ የቦናፓርት አምባገነንነት የበላይነት አገኘ፡፡

አገራችን በተለይም የኢህአድግ ግንባር አባላትና ሌሎች ዲሞክራቶች ሕገመንግሥቱን ሥርዓትን ለመጠበቅ/ልማቱን ለማስቀጠል ሰፊ ግንባር መፍጠር አለባቸው፡፡ በሕገመንግሥት ዙሪያ የሚፈጠረው ግንባር ብዙ ሕዝቦችን ሊያንቀሳቅስ እንደሚችል የሚታመን ነው፡፡

በመጨረሻም አሁንም የኒዮ ሊቨራል ሃይሎች እየተገፋ ወደ ሥልጣን ሊመጡ የሚቋምጡ ቡድኖች የኢትዮጵያን ሕዝብ ድህነት ለማራዘም ካልሆነ በስተቀር ሌላ ጠቀሜታ ስለማይኖረው ሕዝቦች ሊታገሏቸው ይገባል፡፡ የስሜታዊነት ወቅት አልፍዋልና፡፡